የሰ/መ/ቁ. 23363

ግንቦት 26 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ታፈሰ ይርጋ

መድኅን ኪሮስ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት - ነ/ፈጅ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- 1. አቶ ፈርሃን አህመድ - ቀረቡ

2. አቶ አይድድ የሱፍ - ቀረቡ

3. አቶ አብዱልወሃብ አቲዬ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪዎች በሥር 1ኛ ተከሣሽ በመከላከያ ሚኒስቴር የምድር ጦር 103ኛ ሠራዊትና በ2ኛ ተከሣሽ አቶ ገ/እግዚአብሔር ገ/ሕይወት ላይ ባቀረቡት ክስ ንብረትነቱ የ1ኛ ተከሣሽ የሆነውን መኪና 2ኛ ተከሣሽ ሲያሽከረክር ሆድሌ በተባለ ቦታ መስመሩን ጥሎ በመውጣት የ1ኛ ከሣሽን መኪና በመግጨት ከጥቅም ውጭ ያደረገ ስለሆነ የመኪናውን ግምት ብር 219 ሺህ እንዲከፍል፣ እንደዚሁም በዚሁ ግጭት ምክንያት ከጥቅም ውጭ በሆነው ንብረትነቱ የ1ኛ ከሣሽ በሆነው መኪና የ2ኛ ከሣሽ ልጅ ተሳፍሮ ሲጓዝ የሞት አደጋ የደረሰበት ስለሆነና ሟችም ለአካለመጠን ያላደረሱ የ2 ሕፃናት ልጆች አባት ስለነበር እነዚህ 2 ሕፃናት አካለመጠን እስከሚደርሱ እነሱን ለማሳደግና ለመንከባከብ በድምሩ ብር 65,520 /ስልሣ አምስት ሺህ አምስት መቶ ሃያ ብር/ እንደዚሁም ካሣ ብር 74,000 /ሰባ አራት ብር/ በአጠቃላይ ብር 139,520 /መቶ ሰላሣ ዘጠኝ ሺህ አምስት መቶ ሃያ/ እንዲከፈላቸው የጠየቁ ሲሆን 3ኛ ከሳሽም በዚሁ ግጭት የአካል ጉዳት እንደደረሰባቸው ዘርዝረው በድምሩ ብር 140,000 ካሣ ሊከፈለኝ ይገባል በማለት ሶስቱም ከሣሾች በዚህ መልኩ ክሱን ያቀረቡ ሲሆን ተከሣሾች ቀርበው ጉዳቱን አድርሷል የተባለው ተሽከርካሪ በኢትዮጵያ መድን ድርጅት በኩል የመድን ሽፋን የተገባለት መሆኑን ገልፀው በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 43 መሠረት በክርክሩ ጣልቃ ይግባልን በማለት አመልክተው የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ጣልቃ ገብቶ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና ሙሉ መልስ በመስጠት ተከራክሯል፡፡

የኢትዮጵያ መድን ድርጅት በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያነሳው ክርክር ከተከራካሪ ወገኖች መካከል አንደኛው የፌዴራል መንግሥት አካል በሆነ ጊዜና ክስ የቀረበበት የገንዘብ መጠን ከብር 500 ሺህ /አምስት መቶ ሺህ ብር/ በላይ ከሆነ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን ያለው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ስለሆነ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለውም የሚል ነው፡፡

በፍሬ ጉዳዩ ክርክር ረገድም ጣልቃ ገብ የደንበኛው ተሽከርካሪ በ3ኛ ወገን ንብረት ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት ብር 100 ሺህ /አንድ መቶ ሺህ ብር/ እንደዚሁም በሰው ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት የሰጠው ሽፋን እስከ ብር 30 ሺህ /ሰላሣ ሺህ ብር/ ሲሆን በተያዘው ጉዳይ ጉዳት በ2 ሰዎች ላይ ስለደረሰ በድምሩ ብር 60 /ስልሳ ሺህ/ ሺህ እንደዚሁም በንብረት ላይ ለደረሰው ጉዳት በተሰጠው የመድን ሽፋን ልክ ብር 100 ሺህ /አንድ መቶ ሺህ/ ስለሚሆን በአጠቃላይ ብር 160 ሺህ /መቶ ስልሣ ሺህ/ ጣልቃገብ ካሣ ከሚከፍል በስተቀር በክስ የተጠየቀውን በሙሉ ለመክፈል አይገደድም በማለት ተከራክሯል፡፡

ክርክሩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የፍ/ቤቱን የሥረ ነገር ሥልጣን አስመልክቶ በተነሳው መቃወሚያ ላይ ብይን ሳይሰጥ በቀጥታ በፍሬ ጉዳዩ ላይ የተነሣውን ክርክር መርምሮ 1ኛ ከሣሽን በተመለከተ በግጭቱ ምክንያት መኪናው ሙሉ በሙሉ ከጥቅም ውጭ የሆነ ስለሆነ የመኪናውን የዋጋ ግምት ብር 217 /ሁለት መቶ አስራ ሰባት ብር/ ሺህ 2ኛ ከሣሽን በተመለከተም በአደጋው ምክንያት ልጁ ስለሞተ ብር 91,520 /ዘጠና አንድ ሺህ ብር አምስት መቶ ሃያ ብር/ እንደዚሁም 3ኛ ከሣሽን በተመለከተ

ለደረሰበት የአካል ጉዳት ብር 60 ሺ.ህ /ስልሳ ሺ.ህ ብር/ እንዲከፈለው በማለት ውሣኔ ሠጥቷል።

ጣልቃ ገብ በዚህ ውሣኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት አጽንቶታል።

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ ውሣኔ ለማስለወጥ ሲሆን ይህ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል።

ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ ለማየት የሥረ ነገር ሥልጣን ነበረው? ወይንስ አልነበረውም? ሥልጣን አለው ቢባልስ የካሳ ክፍያውን አስመልክቶ የሰጠው ውሣኔ አግባብነት አለውን? የሚለው በመሆኑ በዚሁ መሠረት አቤቱታው ተመርምሯል።

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተም የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህንን ጉዳይ ለመመልከትና ለመወሰን የሥረ ነገር ሥልጣን የለውም ተብሎ መቃወሚያ የቀረበው በአንድ በኩል ጣልቃ ገብ /አመልካች/ የፌዴራል መንግሥት አካል ነው በሚልና በሌላ በኩልም የክርክሩ የገንዘብ መጠን ከብር 500 ሺ.ህ /አምስት መቶ ሺ.ህ ብር/ የሚበልጥ ስለሆነ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለውም በማለት ነው።

ይሁንና የፌዴራል ከፍተኛና የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በክልሎች ካልተቋቋመ የፌዴራል ጉዳዮችን ክልሎች መመልከት እንደሚችሉ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 78/2/ ላይ የተመለከተ ከመሆኑም በላይ የክርክሩ የገንዘብ መጠን ከብር 500 ሺ.ህ /አምስት መቶ ሺ.ህ/ የማይበልጥ ስለሆነ የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን ስላለው በዚህ ረገድ የቀረበው አቤቱታ የሕግ ድጋፍ የሌለው በመሆኑ ችሎቱ አልተቀበለውም።



አመልካች መክፈል የሚገባውን የካሣ መጠን በተመለከተም በንግድ ሕግ ቁጥር 665/2/ ላይ እንደተመለከተው የመድን ገቢው ኃላፊነት በፖሊሲው ላይ ከተመለከተው የገንዘብ መጠን በላይ ሊሆን እንደማይችል የተመለከተ ሲሆን አመልካችም በሰው ላይ ለሚደርስ ጉዳት እስከ ብር 30 ሺ.ህ በ3ኛ ወገን ንብረት ላይ ለሚደርስ ጉዳት ደግሞ እስከ ብር 100 ሺ.ህ /አንድ መቶ ሺ.ህ/ ካሣ ለመክፈል ለሥር 1ኛ ተከሣሽ የመድን ሽፋን መስጠቱን ተገንዝበናል። በዚሁ መሠረትም በአደጋው ጉዳት የደረሰው በ2 ሰዎች እንደመሆኑ መጠን ለእያንዳንዱ ተጎጂ በሽፋኑ መጠን ልክ እንደዚሁም በ3ኛ ወገንም ንብረት ላይ ለደረሰው ጉዳት በመድን ሽፋኑ ልክ ታይቶ ውሣኔ መስጠት ሲገባው ከመድን ሽፋኑ በላይ አመልካች እንዲከፍል በሥር ፍ/ቤቶች መወሰኑ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል።

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. አመልካች በመድን ውሉ መሠረት በ1ኛ ተጠሪ ንብረት ላይ ለደረሰ ጉዳት ብር 100,000 /አንድ መቶ ሺ.ህ/ እንደዚሁም ለ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ለደረሰው የሞትና የአካል ጉዳት ለእያንዳንዳቸው ብር 30,000 /ሠላሣ ሺ.ህ/ በድምሩ ብር 160,000 /አንድ መቶ ስልሳ ሺ.ህ/ የሥር 1ኛ ተከሣሽን በመተካት ይክፈል በማለት የሥር ፍ/ቤቶችን ውሣኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት አሻሽለን ወስነናል።
2. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ።
3. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ነ/ዓ